አንቀጽ፡ ፩፤የሰው፡ ልጅ፡ ሁሉ፡ ሲወለድ፡ ነጻና፡ በክብርና፡ በመብትም፡ እኩልነት፡ ያለው፡ ነው። ፡የተፈጥሮ፡ ማስተዋልና፡ ሕሊና፡ ስላለው፡ አንዱ፡ ሌላውን፡ በወንድማማችነት፡ መንፈስ፡ መመልከት፡ ይገባዋል። አንቀጽ፡ ፪፤እያንዳንዱ፡ ሰው፡ የዘር፡ የቀለም፡ የጾታ፡ የቋንቋ፡ የሃይማኖት፡ የፖለቲካ፡ ወይም፡ የሌላ፡ ዓይነት፡ አስተሳሰብ፡ የብሔራዊ፡ ወይም፡ የኅብረተሰብ፡ ታሪክ፡ የሀብት፡ የትውልድ፡ ወይም፡ የሌላ፡ ደረጃ፡ ልዩነት፡ ሳይኖሩ፡ በዚሁ፡ ውሳኔ፡ የተዘረዘሩት፡ መብቶችንና፡ ነጻነቶች፡ ሁሉ፡ እንዲከበሩለት፡ ይገባል። ከዚህም፡ በተቀረ፡ አንድ፡ ሰው፡ ከሚኖርበት፡ አገር፡ ወይም፡ ግዛት፡ የፖለቲካ፡ የአገዛዝ፡ ወይም፡ የኢንተርናሽናል፡ አቋም፡ የተነሳ፡ አገሩ፡ ነጻም፡ ሆነ፡ በሞግዚትነት፡ አስተዳደር፡ ወይም፡ እራሱን፡ ችሎ፡ የማይተዳደር፡ አገር፡ ተወላጅ፡ ቢሆንም፡ በማንኛውም፡ ዓይነት፡ ገደብ፡ ያለው፡ አገዛዝ፡ ሥር፡ ቢሆንም፡ ልዩነት፡ አይፈጸምበትም። አንቀጽ፡ ፫፤እያንዳንዱ፡ ሰው፡ የመኖር፣፡ በነጻነትና፡ በሰላም፡ የመኖሩ፡ መጠበቅ፡ መብት፡ አለው። አንቀጽ፡ ፬፤ማንም፡ ሰው፡ ቢሆን፡ በባርነት፡ አይገዛም። ፡ባርነትና፡ የባሪያ፡ ንግድም፡ በማንኛውም፡ ዓይነት፡ ክልክል፡ ነው። አንቀጽ፡ ፭፤ማንም፡ ሰው፡ ቢሆን፡ የጭካኔ፡ ስቃይ፡ እንዳይደርስበት፡ ወይም፡ ከሰብዓዊ፡ አፈጻጸም፡ ውጭ፡ የሆነ፡ የተዋረደ፡ ተግባር፡ ወይም፡ ቅጣት፡ አይፈጸምበትም። አንቀጽ፡ ፮፤እያንዳንዱ፡ ሰው፡ በሕግ፡ ፊት፡ በሰው፡ ዘርነቱ፡ የመታወቅ፡ መብት፡ አለው። አንቀጽ፡ ፯፤ሰው፡ ሁሉ፡ በሕግ፡ ፊት፡ እኩል፡ ነው። ፡ያለአንዳች፡ ልዩነትም፡ ሕጉ፡ ደህንነቱን፡ እንዲጠበቅለት፡ እኩል፡ የሆነ፡ መብት፡ አለው። ፡ይህንን፡ ውሳኔ፡ በመጣስ፡ ከሚደረግ፡ ልዩነት፡ ለማድረግ፡ ከሚነሳሳ፡ እንዲጠበቅ፡ ሁሉም፡ የእኩል፡ መብት፡ አለው። ፡አንቀጽ፡ ፰፤እያንዳንዱ፡ ሰው፡ በሕገ፡ መንግስቱ፡ ወይም፡ በሕግ፡ የተሰጡትን፡ መሠረታዊ፡ መብቶች፡ ከሚጥሱ፡ ድርጊቶች፡ ከፍተኛ፡ በሆኑ፡ ብሔራዊ፡ የፍርድ፡ ባለስልጣኖች፡ ፍጹም፡ በሆነ፡ መንገድ፡ እንዲወገድለት፡ መብት፡ አለው። አንቀጽ፡ ፱፤ማንም፡ ሰው፡ ያለፍርድ፡ ተይዞ፡ እንዲታሰር፡ ወይም፡ በግዛት፡ እንዲኖር፡ አይደረግም። አንቀጽ፡ ፲፤እያንዳንዱ፡ ሰው፡ በመብቶቹና፡ በግዴታዎቹ፡ አፈጻጸም፡ እንዲሁም፡ በሚከሰስበት፡ ማንኛውም፡ ዓይነት፡ የወንጀል፡ ክስ፡ ነጻ፡ በሆነና፡ በማያዳላ፡ የፍርድ፡ ሸንጎ፡ በትክክለኛና፡ በይፋ፡ ጉዳዩ፡ እንዲሰማለት፡ የሙሉ፡ እኩልነት፡ መብት፡ አለው። አንቀጽ፡ ፲፩፤በወንጀል፡ ክስ፡ የተከሰሰ፡ ማንኛውም፡ ሰው፡ ለመከላከያው፡ አስፈላጊዎች፡ የሆኑትን፡ ሁሉ፡ አቅርቦ፡ በሚከራከርበት፡ የይፋ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ በሕግ፡ መሠረት፡ ወንጀለኛ፡ መሆኑ፡ እስቲረጋገጥበት፡ ድረስ፡ ከወንጀል፡ ነጻ፡ እንደሆነ፡ የመቆጠር፡ መብት፡ አለው። ማንም፡ ሰው፡ በብሔራዊ፡ ወይም፡ በኢንተርናሽናል፡ ሕግ፡ አንድ፡ ነገር፡ ወንጀል፡ ሆኖ፡ ባልተደነገገበት፡ ጊዜ፡ በፈጸመው፡ ወይም፡ ባልፈጸመው፡ ማንኛውም፡ ሥራ፡ ወንጀለኛ፡ ሆኖ፡ አይከሰስም። ፡ወይም፡ ወንጀሉ፡ በተፈጸመበት፡ ጊዜ፡ ከተደነገገው፡ ቅጣት፡ ይበልጥ፡ አይፈረድበትም። አንቀጽ፡ ፲፪፤ማንም፡ ሰው፡ በግል፡ ኑሮው፡ በቤተሰቡ፡ ውስጥ፡ በቤቱ፡ ወይም፡ በሚጻጻፈው፡ ደብዳቤ፡ በፍርድ፡ ያልተለየ፡ ጣልቃ፡ ገብነት፡ ወይም፡ ክብሩን፡ የሚነካና፡ ስሙን፡ የሚያጎድፍ፡ ተቃውሞ፡ አይፈጸምበትም። ፡እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ከእንደዚህ፡ ያለ፡ ጣልቃ፡ ገብነት፡ ወይም፡ የሚጎዳ፡ ተግባር፡ ሕግ፡ እንዲከላከልለት፡ መብት፡ አለው። ፡አንቀጽ፡ ፲፫፤እያንዳንዱ፡ ሰው፡ በየብሔራዊ፡ ወሰን፡ ክልሉ፡ የመዘዋወርና፡ የመኖር፡ ነጻነት፡ መብት፡ አለው። እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ከማንኛውም፡ አገር፡ ሆነ፡ ከራሱ፡ አገር፡ ወጥቶ፡ እንደገና፡ ወደ፡ አገሩ፡ የመመለስ፡ መብት፡ አለው። አንቀጽ፡ ፲፬፤እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ከጭቆና፡ ሸሽቶ፡ በሌሎች፡ አገሮች፡ ጥገኝነትን፡ የመጠየቅና፡ በደህና፡ የመኖር፡ መብት፡ አለው። ፖለቲካዊ፡ ካልሆኑ፡ ወንጀሎች፡ ወይም፡ የተባበሩት፡ መንግሥታት፡ ድርጅት፡ ዋና፡ ዓላማዎችን፡ ከሚቃረኑ፡ ሥራዎች፡ የተነሳ፡ በሚደርሱ፡ ክሶች፡ ምክንያት፡ ከሆነ፡ ይህ፡ መብት፡ ሊያገለግል፡ አይችልም። አንቀጽ፡ ፲፭፤እያንዳንዱ፡ ሰው፡ የዜግነት፡ መብት፡ አለው። ማንም፡ ሰው፡ ያለፍርድ፡ ዜግነቱ፡ አይወሰድበትም፡ ወይም፡ ዜግነቱን፡ የመለወጥ፡ መብት፡ አይነፈገውም።

አንቀጽ ፡ ፩፤የሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ሲወለድ ፡ ነጻና ፡ በክብርና ፡ በመብትም ፡ እኩልነት ፡ ያለው ፡ ነው ። ፡ የተፈጥሮ ፡ ማስተዋልና ፡ ሕሊና ፡ ስላለው ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ በወንድማማችነት ፡ መንፈስ ፡ መመልከት ፡ ይገባዋል ። አንቀጽ ፡ ፪፤እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የዘር ፡ የቀለም ፡ የጾታ ፡ የቋንቋ ፡ የሃይማኖት ፡ የፖለቲካ ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ ዓይነት ፡ አስተሳሰብ ፡ የብሔራዊ ፡ ወይም ፡ የኅብረተሰብ ፡ ታሪክ ፡ የሀብት ፡ የትውልድ ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ ደረጃ ፡ ልዩነት ፡ ሳይኖሩ ፡ በዚሁ ፡ ውሳኔ ፡ የተዘረዘሩት ፡ መብቶችንና ፡ ነጻነቶች ፡ ሁሉ ፡ እንዲከበሩለት ፡ ይገባል ። ከዚህም ፡ በተቀረ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከሚኖርበት ፡ አገር ፡ ወይም ፡ ግዛት ፡ የፖለቲካ ፡ የአገዛዝ ፡ ወይም ፡ የኢንተርናሽናል ፡ አቋም ፡ የተነሳ ፡ አገሩ ፡ ነጻም ፡ ሆነ ፡ በሞግዚትነት ፡ አስተዳደር ፡ ወይም ፡ እራሱን ፡ ችሎ ፡ የማይተዳደር ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ ቢሆንም ፡ በማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ገደብ ፡ ያለው ፡ አገዛዝ ፡ ሥር ፡ ቢሆንም ፡ ልዩነት ፡ አይፈጸምበትም ። አንቀጽ ፡ ፫፤እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የመኖር፣ ፡ በነጻነትና ፡ በሰላም ፡ የመኖሩ ፡ መጠበቅ ፡ መብት ፡ አለው ። አንቀጽ ፡ ፬፤ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ በባርነት ፡ አይገዛም ። ፡ ባርነትና ፡ የባሪያ ፡ ንግድም ፡ በማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ክልክል ፡ ነው ። አንቀጽ ፡ ፭፤ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ የጭካኔ ፡ ስቃይ ፡ እንዳይደርስበት ፡ ወይም ፡ ከሰብዓዊ ፡ አፈጻጸም ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ የተዋረደ ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ ቅጣት ፡ አይፈጸምበትም ። አንቀጽ ፡ ፮፤እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ በሰው ፡ ዘርነቱ ፡ የመታወቅ ፡ መብት ፡ አለው ። አንቀጽ ፡ ፯፤ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ እኩል ፡ ነው ። ፡ ያለአንዳች ፡ ልዩነትም ፡ ሕጉ ፡ ደህንነቱን ፡ እንዲጠበቅለት ፡ እኩል ፡ የሆነ ፡ መብት ፡ አለው ። ፡ ይህንን ፡ ውሳኔ ፡ በመጣስ ፡ ከሚደረግ ፡ ልዩነት ፡ ለማድረግ ፡ ከሚነሳሳ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ሁሉም ፡ የእኩል ፡ መብት ፡ አለው ። ፡ አንቀጽ ፡ ፰፤እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በሕገ ፡ መንግስቱ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ የተሰጡትን ፡ መሠረታዊ ፡ መብቶች ፡ ከሚጥሱ ፡ ድርጊቶች ፡ ከፍተኛ ፡ በሆኑ ፡ ብሔራዊ ፡ የፍርድ ፡ ባለስልጣኖች ፡ ፍጹም ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ እንዲወገድለት ፡ መብት ፡ አለው ። አንቀጽ ፡ ፱፤ማንም ፡ ሰው ፡ ያለፍርድ ፡ ተይዞ ፡ እንዲታሰር ፡ ወይም ፡ በግዛት ፡ እንዲኖር ፡ አይደረግም ። አንቀጽ ፡ ፲፤እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በመብቶቹና ፡ በግዴታዎቹ ፡ አፈጻጸም ፡ እንዲሁም ፡ በሚከሰስበት ፡ ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ነጻ ፡ በሆነና ፡ በማያዳላ ፡ የፍርድ ፡ ሸንጎ ፡ በትክክለኛና ፡ በይፋ ፡ ጉዳዩ ፡ እንዲሰማለት ፡ የሙሉ ፡ እኩልነት ፡ መብት ፡ አለው ። አንቀጽ ፡ ፲፩፤በወንጀል ፡ ክስ ፡ የተከሰሰ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ለመከላከያው ፡ አስፈላጊዎች ፡ የሆኑትን ፡ ሁሉ ፡ አቅርቦ ፡ በሚከራከርበት ፡ የይፋ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ወንጀለኛ ፡ መሆኑ ፡ እስቲረጋገጥበት ፡ ድረስ ፡ ከወንጀል ፡ ነጻ ፡ እንደሆነ ፡ የመቆጠር ፡ መብት ፡ አለው ። ማንም ፡ ሰው ፡ በብሔራዊ ፡ ወይም ፡ በኢንተርናሽናል ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ወንጀል ፡ ሆኖ ፡ ባልተደነገገበት ፡ ጊዜ ፡ በፈጸመው ፡ ወይም ፡ ባልፈጸመው ፡ ማንኛውም ፡ ሥራ ፡ ወንጀለኛ ፡ ሆኖ ፡ አይከሰስም ። ፡ ወይም ፡ ወንጀሉ ፡ በተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ ከተደነገገው ፡ ቅጣት ፡ ይበልጥ ፡ አይፈረድበትም ። አንቀጽ ፡ ፲፪፤ማንም ፡ ሰው ፡ በግል ፡ ኑሮው ፡ በቤተሰቡ ፡ ውስጥ ፡ በቤቱ ፡ ወይም ፡ በሚጻጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ በፍርድ ፡ ያልተለየ ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ወይም ፡ ክብሩን ፡ የሚነካና ፡ ስሙን ፡ የሚያጎድፍ ፡ ተቃውሞ ፡ አይፈጸምበትም ። ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ከእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ወይም ፡ የሚጎዳ ፡ ተግባር ፡ ሕግ ፡ እንዲከላከልለት ፡ መብት ፡ አለው ። ፡ አንቀጽ ፡ ፲፫፤እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በየብሔራዊ ፡ ወሰን ፡ ክልሉ ፡ የመዘዋወርና ፡ የመኖር ፡ ነጻነት ፡ መብት ፡ አለው ። እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ከማንኛውም ፡ አገር ፡ ሆነ ፡ ከራሱ ፡ አገር ፡ ወጥቶ ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ የመመለስ ፡ መብት ፡ አለው ። አንቀጽ ፡ ፲፬፤እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ከጭቆና ፡ ሸሽቶ ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ ጥገኝነትን ፡ የመጠየቅና ፡ በደህና ፡ የመኖር ፡ መብት ፡ አለው ። ፖለቲካዊ ፡ ካልሆኑ ፡ ወንጀሎች ፡ ወይም ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ዋና ፡ ዓላማዎችን ፡ ከሚቃረኑ ፡ ሥራዎች ፡ የተነሳ ፡ በሚደርሱ ፡ ክሶች ፡ ምክንያት ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ መብት ፡ ሊያገለግል ፡ አይችልም ። አንቀጽ ፡ ፲፭፤እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የዜግነት ፡ መብት ፡ አለው ። ማንም ፡ ሰው ፡ ያለፍርድ ፡ ዜግነቱ ፡ አይወሰድበትም ፡ ወይም ፡ ዜግነቱን ፡ የመለወጥ ፡ መብት ፡ አይነፈገውም ።